የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፪<br>አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 14th Year No 52.<br>ADDIS ABABA 11th August, 2008 |

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፬/፪ሺ ዓ.ም

ለጣና እና ለበለስ የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፬ሺ፩፻፺

CONTENTS

Proclamation No. 594/2008

International Development Association Financing Agreement for the Tana and Beles Integrated Water Resources Development Project Ratification Proclamation Page 4190

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፬/፪ሺ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጣና እና ለበለስ የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፳፯ሚሊዮን፬፻ሺ ኤስ.ዲ.አር /ሀያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፬ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና ፲፪ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጣና እና ለበለስ የተቀናጀ የውሃ ሀብት ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፬/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 594/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCR-ATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTER NATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 27,400,000 SDR (twenty seven million four hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Tana and Beles Integrated Water Resources Development Project was signed in Addis Ababa on the 13th day of June 2008;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the agreement at its session held on the 1st day of July, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Sub-Article (1) and (12) of Article 55 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Tana and Beles Integrated Water Resources Development Project Ratification Proclamation No. 594/2008".

## ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፫ ቀን ፪ሺ፰ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 4457-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. <u>የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፯ሚሊዮን፬፻ሺ ኤስ.ዲ. አር /ሀያ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Financing Agreement Credit Number 4457-ET signed in Addis Ababa on the 13th day of June 2008 between of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 27,400,000 SDR (twenty seven million four hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of August, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**